የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የሳምንታዊ መረጃ ማሰራጫ

# ሳምንታዊ የቢዝነስ መረጃዎች

(ሚያዝያ 21- 28/2016 ዓ.ም)
April 29-May 6/2024

**በኮርፖሬት ኮሙኒኬሽንና ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ**

1. **አርሶ አደሮች የብድር አቅርቦት የሚያገኙበት መዋቅር ሊዘረጋ ነው**

ግብርና ሚኒስቴር ከትንሽ እስከ ትልቅ ደረጃ ላይ የሚገኙ አርሶ አደሮች የብድር አቅርቦት በቀላሉ እንዲያገኙ ትላልቅ የፋይናንስ ተቋማት የተካተቱበት መዋቅር ሊዘረጋ መሆኑን አስታወቀ፡፡

***ሪፖርተር፡ May 1, 2024***

በግብርና ሚኒስቴር አስፈጻሚነት ተግባራዊ በሚደረገው አዲሱ አሠራር ላይ ብሔራዊ ባንክ፣ ገንዘብ ሚኒስቴር፣ የማይክሮ ፋይናንስና ንግድ ባንኮች የተካተቱበት መሆኑ ታውቋል፡፡

ሚኒስቴሩ ይህንን ያስታወቀው የፋይናንስ ተቋማት ለግብርና ዘርፉ እያደረጉ ያሉትን አስተዋጽኦ በተመለከተ ከተለያዩ የፋይናንስ ተቋማት ከተውጣጡ ኃላፊዎች ጋር ማክሰኞ ሚያዝያ 22 ቀን 2016 ዓ.ም. ውይይት ባደረገበት ወቅት ነው፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/129136/

2. **የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት ሙስናን ለመከላከልና ከሀገር የሸሹ ሀብቶችን ለማስመለስ በጋራ መስራት እንዳለባቸው ተገለጸ**

የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት በሙስና ከሀገር የሸሹ ሀብቶችን ለማስመለስና ግልፅነት የሰፈነበት አሰራርን ለመተግበር ትብብርን ማጎልበት እንደሚገባቸው የምስራቅ አፍሪካ የጸረ-ሙስና ኮሚሽኖች ማህበር ፕሬዚዳንት ኒሪሪ ማዲሊ ገለጹ።

የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት የጸረ-ሙስና ኮሚሽኖች ማህበር የተመዘበሩና ከሃገር የሸሹ ሃብቶችን በቅንጅት ማስመለስ ላይ ያተኮረ ጉባኤ በአዲስ አበባ አካሂዷል።

**ኢዜአ፡ ሚያዝያ 24/2016**

በመድረኩ ኢትዮጵያን ጨምሮ ስምንት የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት የጸረ ሙስና የስራ ዘርፍ ኃላፊዎችና ተወካዮች ተገኝተዋል።

በውይይቱ በሙስና የሚሸሹና የሚመዘበሩ ሀብቶችን ለማስመለስ በትብብር መስራት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ወሳኝ ጉዳይ መሆኑ ተነስቷል።

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_4386918

3. ***ከከበሩ ማዕድናት የበለጠ ተጠቃሚ ማድረግ የሚያስችለው ስትራቴጂ***

በዓለም ላይ በርካታ ዓይነት የከበሩ ማዕድናት አሉ፡፡ ማዕድናቱ በተፈጥሮ ለሰው ልጆች የተሰጡ ገጸ በረከቶች እንደመሆናቸው ከጥንት ጀምሮ በሰዎች ዘንድ ተወዳጅ ሆነው ዘልቀዋል፡፡ በተለይ እንደ ኦፓል፣ ሳፋየር፣ ሩቢ እና ኤመራልድ ያሉት የከበሩ ማዕድናት በጣም ተወዳጅ ከሆኑ የከበሩ ማዕድናት መካከል ይጠቀሳሉ፡፡

**Ethiopian press agency May 3, 2024**

ማዕድናቱ በተለያዩ የጌጣጌጥ ዓይነቶች በሚፈለገው ቅርጽና ዲዛይን ተሰርተው ለአንገት፣ ለጆሮ፣ ለጣት፣ ለእግርና ለሌሎችም ጌጣጌጥነት እንዲውሉ ይደረጋሉ፡፡ ጌጣጌጦቹም በስጦታ መልኩ የሚበረከቱ ውድ ቁሶች እንደመሆናቸው በሰዎች ዘንድ ልዩ ዋጋና ትርጉም ተሰጥቷቸዋል፡፡

https://press.et/?p=127095

4. **የግብርና ዘርፍ የመድን ዋስትና የተበታተነና ባለቤትነቱ የማይታወቅ እንደሆነ ተገለጸ**

የግብርና ዘርፍ የመድን ዋስትናን የሚያስፈጽመው አካል ማን እንደሆነ በግልጽ ስለማይታወቅ፣ አሠራሩ ባለቤት አልባና የተበታተነ እንደሆነ የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

***Reporter May 5, 2024***

የግብርና ሚኒስቴር የኢንቨስትመንትና ግብዓት ዘርፍ ሚኒስትር ደኤታ ሶፊያ ካሳ (ዶ/ር) እንደገለጹት፣ በግብርና ዘርፍ የሚሰጠውን የመድን ዋስትና ለመምራት ሚኒስቴሩ የራሱ የሆነ የሕግ ማዕቀፍ ስለሌለው አርሶ አደሮች በየቦታው የተንጠባጠበ የመድን አገልግሎት እየተሰጣቸው ነው፡፡

**https://www.ethiopianreporter.com/129233/**

5. **የንግድ ዘርፉ ለውጭ ባለሀብቶች መከፈቱ የሚያስገኘው ፋይዳ**

ኢትዮጵያ ለውጭ ኩባንያዎች ዝግ አድርጋቸው የነበሩ የተለያዩ የቢዝነስ ዘርፎችን እየከፈተች ነው፡፡ በቅርቡም መንግሥት ለዘመናት ኢትዮጵያዊያን ብቻ ይሳተፉበት የነበረውን የአገር ውስጥ የጅምላና ችርቻሮ ንግድ እንዲሁም የወጪና ገቢ ንግድ የውጭ ኩባንያዎች እንዲገቡበት ክፍት አድርጓል። ይህንን ድንገተኛ የመንግሥት ውሳኔም በርካቶች ያልተጠበቀ ሲሉ እየገለጹት ይገኛሉ።

***Reporter May 5, 2024***

መንግሥት እነዚህን አራት የቢዝነስ ዘርፎች ማለትም የአገር ውስጥ የጅምላና ችርቻሮ ንግድ እንዲሁም የወጪና ገቢ ንግድ ለውጭ ኩባንያዎች ክፍት ለማድረግ መወሰኑ ከባድ መሆኑን የገለጹ አንድ የኢኮኖሚ ባለሙያ፣ ይህ ውሳኔ መንግሥት ከዚህ በኋላ ለኢትዮጵያውያን ባለሀብቶች ወይም የንግድ ተዋናዮች ከለላ እንደማይሰጥ እንቅጩን የተናገረበት ነው ሲሉ ይገልጹታል።

**https://www.ethiopianreporter.com/129269/**

6. **ኢሰማኮ የሠራተኞች የደመወዝ ግብር እንዲቀነስና ዝቅተኛ የደመወዝ ወለል እንዲወሰን ሊጠይቅ ነው**

የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን ከጠቅላይ ሚኒስትር ዓብይ አህመድ (ዶ/ር) ጋር አድርጎት በነበረው ውይይት አስቸኳይ ምላሽ ይሻሉ ብሎ ያቀረባቸው ዋና ዋና ጥያቄዎች እስካሁን ምላሽ እንዳላገኙ አስታወቀ።

***Reporter May 1, 2024***

ኢሰማኮ በዓለም አቀፍ ደረጃ ረቡዕ ሚያዚያ 23 ቀን የሚከበረውን የሠራተኞች ቀን አስመልክቶ በሰጠው መግለጫ ከበርካታ ወራቶች በፊት ከጠቅላይ ሚኒስትር ዓብይ ጋር የኢትዮጵያ ሠራተኞች ያሉባቸውን መሠረታዊ ችግሮች ለመፍታት ያለመ ውይይት ማድረጉን አስታውሷል።

**https://www.ethiopianreporter.com/129207/**

7. **የተወሰነ ድርሻቸውን ለሕዝብ የሚሸጡ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተለዩ**

በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ላይ የተወሰ ድርሻቸውን ለሕዝብ የሚሸጡ ስድስት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች መለየታቸውን የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ (Ethiopian Investment Holdings – EIH) ኃላፊዎች ገለጹ፡፡

***Reporter May 1, 2024***

ኢትዮጵያ የካፒታል ገበያን መጀመር አስመልክቶ የተወሰኑ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች (State Owned Enterprises) ውስን ድርሻዎቻቸውን በኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ላይ እንደሚሸጡ ሲገለጽ መቆየቱ ይታወሳል፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/129152/

## 8. በአዲስ አበባ በሚካሄደው የኢትዮጵያ ታምርት ኤክስፖ 200 አምራች ኢንዱስትሪዎች ይሳተፋሉ

ከግንቦት 1 /2016 ጀምሮ ለአምስት ተከታታይ ቀናት በአዲስ አበባ በሚካሄደው የኢትዮጵያ ታምርት ኤክስፖ 200 አምራች ኢንዱስትሪዎች እንደሚሳተፉ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ።

**ኢዜአ: ሚያዝያ 24/20216**

ኤክስፖው የኢንዱስትሪዎችን የምርታማነት አቅም በማሳየት 3 ቢሊየን ብር የሚገመት የገበያ ትስስር መፍጠር እንደሚያስችል ተገልጿል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ዴኤታ ታረቀኝ ቡሉልታ፤ የኢትዮጵያ ታምርት ኤክስፖን አስመልክተው ለመገናኛ ብዙኃን መግለጫ ሰጥተዋል።

**https://www.ena.et/web/amh/w/amh_4385663**

# *በውጭ ቋንቋዎችና ከውጭ ሚዲያዎች*

## 9. Why poultry farmers are ill at ease with Kenya-US trade negotiations

Kenya's poultry farmers say the country risks becoming a dumping ground for US poultry and dairy products, as Nairobi and Washington work on a deal.

**THE EASTAFRICAN MAY 05 2024**

Last week, poultry farmers raised fears that the US-Kenya Strategic Trade and Investments Partnership (Stip) agreement would allow cheap poultry imports; likely to result in the loss of Ksh172 billion ($1.3 billion) annually if implemented.

**https://www.theeastafrican.co.ke/tea/business/why-poultry-farmers-are-ill-at-ease-with-kenya-us-trade-4612670**

## 10. South Korea dangles 'tailored' support ahead of its first-ever Africa summit

Rice may not be a staple in most of East Africa, but it is one of the most consumed cereals in the region.

Koreans know it, so, over the past couple of years, they have introduced a technology for higher-yielding seed, known as K-Rice.

In East Africa, Kenya and Uganda have been pilot sites, although the K-Rice Belt is wider on the continent, including Senegal, Gambia, Guinea Bissau, Guinea, Ghana and Cameroon. The project helped produce 2,040 tonnes of seed in 2023.

**THE EASTAFRICAN MAY 05 2024**

The Koreans say the summit is not just about rice or food. They say they have invited all African heads of state and government to pitch their preferred kind of cooperation.

Chung Byung-won, South Korea's Deputy Minister for Political Affairs in the Ministry of Foreign Affairs, said there will be something new for Africa.

https://www.theeastafrican.co.ke/tea/news/world/south-korea-dangles-tailored-support-ahead-of-africa-summit-4612494

## 11. Ethiopian Airlines expects 30pc passengers surge in 2024, CEO Mesfin Bekele says

Ethiopian Airlines expects to carry 30 percent more passengers in the year ended June from the year before, its chief executive told Reuters on Wednesday, buoyed by new routes and a rebound in global travel.

**THE EASTAFRICAN MAY 1 2024**

Africa's biggest airline, however, faces risks from delayed aircraft deliveries and the grounding of some planes due to engine shortages caused by supply chain disruptions, Mesfin Tasew Bekele said in an interview.

https://www.theeastafrican.co.ke/tea/business/ethiopian-airlines-sees-30pc-surge-in-passengers-in-2024-4609528

## 12. Measures taken to drive macro economy safely

**The Ethiopian government has implemented various measures to address the macroeconomic imbalances and challenges faced by the country's economy. However, the outcomes of these measures have fallen short of expectations. The global economic crisis, as well as domestic conflicts, has posed additional obstacles to achieving the desired targets.**

**Ethiopian herald May 5, 2024**

Four years ago, the government introduced a home-grown economic reform program with the objective of addressing long-standing economic anomalies. The reform program aimed to tackle structural and multidimensional challenges that have hindered the country's economic growth.

**https://press.et/herald/?p=95187**

## 13. Ethiopia Markets Business Opportunities in Agriculture, Sustainable Agro Logistics, Energy

Ethiopia used the Netherlands-Africa Business Council (NABC) event to market its business opportunities in agriculture, sustainable agro logistics and energy.

The Ethiopian Delegation led by Deputy Commissioner of Ethiopian Investment Commission Dagato Kumbe took part at NABC event, 'AFRICA 20 Works! 24' held in Amsterdam, Netherlands.

**EBC APRIL28, 2024**

The event was held under the theme "Africa's Green Industrialisation - Made in Africa" at Royal Tropical Institute (KIT), according to Ethiopian Embassy in Brussels.

**https://ebc.et/english/newsdetails.aspx?newsid=6565**